'አጎቴ ሆይ! በርሷ ምክንያት አላህ ዘንድ የምሟገትልህን ቃል ላኢላሃ ኢለሏህ በል!'

ሰዒድ ቢን ሙሰየብ ከአባታቸው እንዳስተላለፉት እንዲህ አሉ፦ "አቡ ጧሊብን ሞት የቀረባቸው ጊዜ የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወደርሳቸው መጡ። አቡጧሊብ ዘንድም አቡጀህልንና ዐብደላህ ቢን አቢ ኡመያህ ቢን ሙጚራን አገኙ። ለአቡጧሊብም እንዲህ አሉ 'አጎቴ ሆይ! በርሷ ምክንያት አላህ ዘንድ የምሟገትልህን ቃል ላኢላሃ ኢለሏህ በል!' አቡጀህልና ዐብደላህ ቢን አቢ ኡመያህም 'ከዐብዱልሙጦሊብ መንገድ ትሸሻለህን?!' አሉ። አቡጧሊብም የመጨረሻው ንግግሩ 'በዐብዱል ሙጦሊብ መንገድ ላይ ነኝ!' እስኪል ድረስ የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በአቡጧሊብ ላይ (እንዲሰልም ሀሳብ) ከማቅረብ እነ አቡጀህልም እነዚህን ቃላቶች ከመደጋገም አልተወገዱም። አቡጧሊብ 'ላኢላሃ ኢለሏህ' ከማለት እምቢተኛ ሆነ። የአላህ መልክተኛም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) 'በአላህ እምላለሁ! እስካልተከለከልኩ ድረስ ምህረትን
እጠይቅልሃለሁ።' አሉ። አላህም {ለነቢዩና ለነዚያ ላመኑት ለአጋሪዎቹ ምህረትን ሊለምኑ የሚገባ አልነበረም።} [አት-ተውባህ:
113] የሚለውን አወረደ። አላህ በአቡ ጧሊብ ዙሪያም ለአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ በማለት አወረደ {አንተ የወደድከውን ሰው ፈፅሞ አታቀናም። ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያቀናል።} [አልቀሶስ:56]"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አጎታቸው አቡጧሊብ ዘንድ ጣእረሞት ላይ ሳለ ገቡና እንዲህ አሉት: አጎቴ ሆይ! በርሷ ምክንያት አላህ ዘንድ የምመሰክርልህን ቃል "ላኢላሃ ኢለሏህ" በል። አቡጀህልና ዐብደላህ ቢን አቢኡመያህም "አቡጧሊብ ሆይ! የአባትህ የዐብዱልሙጦሊብን መንገድ ትተዋለህን?!" አሉ። የጣኦት አምልኮዋቸውን ለማለት ነው። አቡጧሊብ በመጨረሻ ንግግራቸው ላይ "በዐብዱል ሙጦሊብ መንገድ ላይ ነኝ!" እስኪሉ ድረስም ይህን ከመጎትጎት አልተወገዱም። ይህም የሺርክና የጣኦት አምልኮ መንገድ ነው። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) "ጌታዬ እስካልከለኝ ድረስ ምህረትን እለምንልሃለሁ።" አሉ። ይህ የአላህ ንግግርም ወረደ: {ለነቢዩና ለነዚያ ላመኑት ለአጋሪዎቹ የዝምድና ባለቤቶች ቢሆኑም እንኳ እነሱ (ከሀዲዎቹ) የእሳት ጓዶች መሆናቸው ከተገለፀላቸው በኋላ ምህረትን ሊለምኑ የሚገባ አልነበረም።} [አት-ተውባህ: 113] በአቡ ጧሊብ ዙሪያም ይህ የአላህ ንግግር ወረደ: {አንተ የወደድከውን ሰው ፈፅሞ አታቀናም። ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያቀናል። እርሱም ቅኖቹን አዋቂ ነው።} [አልቀሶስ: 56]" አንተ መቃናቱን የወደድከውን ሰው አታቀናም። በአንተ ላይ ያለው ግዴታ ማድረስ ብቻ ነው። አላህ የሻውን ያቀናል።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/3410